# መመርያ የMONTGOMERY COUNTY የትምህርት ቦርድ

| | |
|---|---|
| ከዚህ ጋር የተዛመዱ ርእሶች፡ | ACF, ACF-RA, COB-RA, GME-EA, IOH-RA, IJA-RA, IRB-EA, IRB-RA, JGB-EA, JHC-RA, JHF, JHF-RA, JOA-RA |
| ሀላፊው ፅ/ቤት፣ | የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል<br>የሰው ሀይልና እድገት<br>ልዩ ትምህርት እና የተማሪ አገልግሎቶች<br>የተዛመዱ ምንጮች፡ የተመዘገበ የሜሪላንድ ኮድ/ህግ Education Article (የትምህርት አንቀፅ) §6-113, Family Law Article (የቤተሰብ ህግ አንቀፅ) §§5-560, 5-561, 5-701, 5-702, 5-705.2, 5-704, 5-705, 5-708, እና Human Services Article (የሰብአዊ አገልግሎቶች አንቀፅ) §1-202; *Code of Maryland Regulations*/የሜሪላንድ ደንቦች ኮድ 07.02.07.04-.05፣ 13A.12.05.02፣ እና 13A.08.01.03 |

## የልጅ ማጎሳቆል እና ቸልተኝነት

## A. ዓላማ[1]

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) ስለ ሁሉም ተማሪዎች ሰላም እና አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ እና ስሜታዊ ደህንነት ያለውን ግዴታ አሁንም ያረጋግጣል። የቦርዱ እምነት ሁሉም ልጆችና ደካማ አዋቂዎች ከማጎሳቆልና ከቸልተኝነት የመጠበቅ መብት አላቸው የሚል ነው። የልጆችና የደካማ አዋቂዎች ማጎስቆልና ቸልተኝነትን ለይቶ ለማወቅ፣ ዘገባ ለማዘጋጀት፣ እና ለመከላከል ሁለገብ አቀራረብ/አያያዝ ቦርዱ ሙሉ በሙሉ ይደግፋል። በተጨማሪ፣ Montgomery County Public Schools (MCPS) ስለ ልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት በወላጆች/አሳዳጊዎች እና በሰፊው ማህበረሰብ መካከል ግንዛቤ ከፍ እንዲል ሊጫወት ስለሚችለው ልዩ ሚና ቦርዱ ያውቅለታል። ለዚህም አላማ፣ ለሚከተሉት ስርአት ያለው ፕላን የማዘጋጀትና የመተግበርን አስፈላጊነት ቦርዱ ያሰምርበታል—

1. ሁሉም ሰራተኞች በጠባያቸው ከሁሉም የላቁ ስነምግባራዊ መመዘኛዎችን መገንዘባቸውንና ለነሱ ተጠያቂ መሆናቸውን፣ እንዲሁም የተጠረጠረን የልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት የመለየት፣ ዘገባ የማቅረብ፣ በህጋዊ ሀላፊነቶች እና የመከላከል ሞራላዊ ግዴታቸውን አጥብቀው መገኘታቸውን ማረጋገጥ፤

---

[1] Regulation (ደንብ) JHC-RA, *Child Abuse and Neglect*/የልጅ መጎሳቆልና ቸልተኝነት {15}፣ በዚህ መመርያ ጥቅም ላይ የዋሉትን የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ ይዟል፡- ማጎሳቆል፤ ቸልተኝነት፤ በት/ቤት የሚፈፀሙ የልጅ ማጎሳቆል ግንኙነቶች፤ ልጅ፤ ደካማ አዋቂ፤ የMCPS ሰራተኞች፤ የMCPS ስራ ተቋራጮች፣ የMCPS በጎ-ፈቃደኞች፤ እና የMCPS ንብረት።

2. Montgomery County State's Attorney's Office/ የስቴት አቃቤ ፅ/ቤት፣ Montgomery County Police Department/የፖሊስ መምርያ (MCPD)፣ እና በMontgomery County Department of Health and Human Services/ጤናና ህዝባዊ አገልግሎቶች መምርያ (MCDHHS) Child Welfare Services/የልጅ ደህንነት አገልግሎቶች፣ በዘልምድ Child Protective Services/የልጅ መከላከያ አገልግሎቶች (CPS) ተብለው የሚጠሩ፣ እንዲሁም ሌሎች የውጭ ወኪል ድርጅቶችን የሚያካትቱ የMontgomery County (County) ሽሪክ ወኪል ድርጅቶች በማጎሳቆል እና/ወይም በቸልተኝነት በተጠረጠሩ በሚካሄዱ ምርመራዎች ሙሉ በሙሉ መተባበር፤

3. ከካውንቲ ተባባሪ ወኪል ድርጅቶች ጋር በመሆን፣ የማጎሳቆል እና/ወይም የቸልተኝነት ተጠቂዎች ናቸው ተብለው ለሚጠረጠሩ ልጆችና ደካማ አዋቂዎች ድጋፍ መስጠት፤

4. በMCPS ንብረት ላይ ለሚገኙ ልጆች ቀጠተኛ፣ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ፣ እና መረን የሌለው ግንኙነት ላላቸው አዳዲስና ነባር ሰራተኞች እንዲሁም በጎ-ፈቃደኞችና የውጭ ስራ ተቋራጮችን ለማጣራት የሰው ሀይል ማስተዳደር ስርአቶችና ሂደቶችን ማበልፀግ፤

5. ከብሄራዊና የአካባቢ ባለሙያዎች ድጋፍ ማጎሳቆልና ቸልተኝነትን እጅጉን ወቅታዊ በሆኑ የመለያ፣ ዘገባ የማቅረብያ እና የመከላከያ ልምዶች አማካይነት ለMCPS ሰራተኞች ሞያዊ ብልፅግና መተለም፤

6. ማጎሳቆልና ቸልተኝነትን በመከላከልና በማስታወቅ ቀልጣፋና ጠንካራ፣ ከእድሜ ጋር የተቀናጁ የመማር እድሎች በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ማቅረብ፤ እናም

7. የልጆችና የደካማ አዋቂዎች ማጎሳቆልና ቸልተኝነትን ለማወቅ፣ ለማስታወቅ፣ እና ለመከላከል ንቃትን ለማበልፀግ ለወላጆች፣ የውጭ ስራ ተቋራጮች፣ በጎ-ፈቃደኞች፣ እና ለሰፊው ህብረተሰብ እድሎች ማቅረብ።

B. አቋም

1. ለተጠረጠረ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት ዘገባ ማቅረብና ምላሽ መስጠት

a) ከCounty ሽሪክ ወኪል ድርጅቶች ጋር በመተባበር በዳበሩ የዘገባ አቀራረብ መመርያዎች መሰረት፣ ሁሉም የMCPS ሰራተኖች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች ማንኛውንም የተጠረጠሩ የማጎሳቆል እና/ወይም የቸልተኝነት ክውነወቶች/ምሳሌዎች በግልና በቀጥታ ማስታወቅ ይፈለግባቸዋል። የተባለን ጾታዊ አመፅ የሚያካትቱ የተጠረጠሩ የማጎሳቆል ክውነወቶች ደህንነትን ለማራመድ፣ የMCPS እና የCounty ሽሪክ ወኪል ድርጅቶች ለMCPD Special Victims Investigations Division/የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል ፈጣን ማስታወቂያ መስጠትን የሚያቀላጥፉ ተጨማሪ መመርያዎች ያዘጋጃሉ።[2]

[2] የተጠረጠሩ የደካማ አዋቂዎች የማጎሳቆል እና/ወይም የቸልተኝነት ጉዳዮች በMCDHHS ውስጥ ለሚገኘው ለAging and Disabilities Services Information and Assistance Unit/የሽምግልናና የአካል ስንክልና አገልግሎቶች የመረጃና የድጋፍ ጓድ ዘገባ ያቀርባሉ።

b) ለተጠረጠረ ማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት ዘገባው መቅረብ እንዳለበት ወይም እንደሌለበት ግለሰቡ/ቧ የመጠራጠር ሁኔታ ካጋጠመው/ማት ዘገባውን ለCPS የማቅረብ እርምጃ ይወስዳል/ትወስዳለች።

c) ዘገባውን ለCPS ከማቅረብ በፊት የተጠረጠረን ማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት ጉዳይ መመርመር ወይም ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ሚና አይደለም።

d) የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች የተጠረጠረን ማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት በCPS፣ MCPD ወይም በሌላ የውጭ ወኪል ድርጅት ምርመራ የሚያዘባ ማንኛውንም ድርጊት መፈፀም የለባቸውም።

e) በMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ተፈፀመ ተብሎ በሚጠረጠር የልጅ ማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት በእያንዳዱ ጉዳይ የሚከተሉት ተጨማሪ ሂደቶች ይተገበራሉ፡

(1) አግባብ ያላቸው የMCPS ፅ/ቤቶችና ሽሪክ ወኪል ድርጅቶች አጥቂ ነው የሚባለው በተጠቂ ነው ተባዩና በሌሎች ተማሪዎች ደህንነት የቅርብ አደጋ እንዳይሆን ያረጋግጣሉ።

(2) እንደነዚህ አይነቶቹ ጉዳዮች የቦርድ መመርያዎች፣ የMCPS ደንቦች፣ ውሎች፣ እና/ወይም ሌላ መመርያ እምቅ ጥሰቶችን ሊያካትቱ ስለሚችሉ፣ አግባብ ካላቸው የቦርድ መመርያዎችና የMCPS ደንቦች ጋር ስምሙ የሆነ የውስጥ ምርመራ በMCPS ይከናወናል። የሆነ ሆኖ፣ በማንም የውጭ ወኪል ድርጅቶች ምርመራዎች በሚካሄዱበት ወቅት፣ ከመርማሪ ወኪል ድርጅት ጋር ተቀዳሚ ስምምነት ከሌለ ወይም ያቀረባቸው ገደቦች የሚከተል ካልሆነ፣ MCPS ምስክሮችን፣ ተጠቁ የተባሉትን፣ ወይም ጥቃት ፈፃሚዎችን ቃለ መጠየቅ ማድርግ አይችልም። በተጨማሪ፣ MCPS ሁሉንም የውስጥ ምርመራዎች ምርመራ በማካሄድ ላይ ከሚገኝ የውጭ ወኪል ድርጅት ጋር ሙሉ በሙሉ በመተባበር እና በውጩ ምርመራ ጣልቃ በማይገባ ወይም በማያደናቅፍ ዘዴ ማካሄድ አለበት።

2. ምስጢራዊነት፣ ከተጠያቂነት ነፃ መሆን፣ ከበቀል መጠበቅ

a) ማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት በቀና መንፈስ ዘገባ የሚያዘጋጅ ወይም በዝግጅት የሚሳተፍ ወይም በተከታይ የዳኝነት ሂደት የሚሳተፍ ማንኛውም ግለሰብ በሜሪላንድ ህግ መሰረት የማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት ዘገባ በማቅረብ ወይም በምርመራ ወይም በተከታይ የዳኝነት ሂደት በመሳተፍ ሊደርስ ከሚችል የፍትሃብሄር ወይም የወንጀል ቅጣት ነፃ ነው።

b) ማንም የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ሆን ብሎ የማጎሳቆልና ቸልተኝነት ዘገባ አሰራር አያግድም ወይም ጣልቃ አይገባም።

c) የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች ተነሳስተው የማጎሳቆል እና/ወይም የቸልተኝነት የቀና መንፈስ ዘገባዎች ሲያዘጋጁ ወይም በማጎሳቆል እና/ወይም በቸልተኝነት ምርመራ ሲሳተፉ፣ MCPS በነዚህ ድርጊቶች ምክንያት ሊደርስባቸው ከሚችል ማስፈራራት፣ ወከባ፣ ወይም ግብረመልሶች/ቂም በቀል ሊከላከልላቸው ይጥራል።

d) ተማሪዎች የማጎሳቆል እና/ወይም የቸልተኝነት ተጠቂዎች ወይም ምስክሮች ሲሆኑ ወይም ተነሳስተው የማጎሳቆል እና/ወይም የቸልተኝነት የቀና መንፈስ ዘገባዎች ሲያዘጋጁ ወይም በማጎሳቆል እና/ወይም በቸልተኝነት ምርመራ ሲሳተፉ፣ MCPS በነዚህ ድርጊቶች ምክንያት ሊደርስባቸው ከሚችል ማስፈራራት፣ ወከባ፣ ወይም ግብረመልሶች/ቂም በቀል ሊከላከልላቸው ይጥራል።

e) የተጠረጠረ ማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት የሚመለከቱ መዛግብት ወይም ዘገባዎች ሳይፈቀድ አውጥቶ ለሌላ ማሳወቅ በሜሪላንድ ህግ መሰረት በወንጀል የሚያስጠይቅ ነው። በተጨማሪ፣ ሁሉም የMCPS ሰራተኞች፣ በጎ-ፈቃደኞች፣ እና ስራ ተቋራጮች፣ በህግ እስካልተጠየቁ ድረስ የዘገባ አቅራቢውን ማንነት የመጠበቅ ሀላፊነት አለባቸው።

3. ሆን ብሎ የማጎሳቆል እና/ወይም የቸልተኝነት ዘገባ አለማቅረብ ወይም በዘገባ ዝግጅት ጣልቃ መግባት የሚያስከትሏቸው ውጤቶች

ማንኛውም የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ለMCPS በሞያ ወይም በአገልግሎት ችሎታቸው እየሰሩ፣ የልጅ ማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት አውቆ ዘገባ ከማቅረብ የተቆጠበ፣ ወይም ሆን ብሎ ዘገባ የከለከለ ወይም በዘገባ ጣልቃ የገባ፣ እንደአግባቡ እስከ እና በማካተት በፅ/ቤት ስለተፈፀመ ጉድለት መታገድ ወይም መሰናበት፣ የስራ ተቋራጭነት አገልግሎቶች መቋረጥ፣ ወይም የበጎ-ፈቃደኛ ልዩ መብቶች መቋረጥ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበ(ባ)ታል። በተጨማሪ፣ ማንኛውም በMaryland State Board of Education/የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቦርድ (MSDE) ወይም ሌላ የስራ ፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት ሰጪ ቦርድ ስልጣን ስር የተሰጠ ማንኛውም ምስክርነት፣ በሜሪላንድ ህግ በተቀመጡ መመዘኛዎች መሰረት፣ ሊታገዱ ወይም ሊነሱ/ሊሰረዙ ይችላሉ።

4. ማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት በሚመለከት የተፈፀሙ አመፆች የሚያስከትሏቸው ውጤቶች

የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ በማጎሳቆል እና/ወይም በቸልተኝነት ውስጥ ተካትቷል ወይም የቦርድን መመርያዎች፣ የMCPSን ደንቦች፣ ወይም መመርያዎች ጥሷል ብሎ MCPS ከወሰነ፣ ግለሰቡ በስራ ላይ የስነምግባር መጓደል ምክንያት የመታገድ ወይም የመሰናበት፣ ወይም የአገልግሎቶች ወይም የበጎ-ፈቃድ ልዩ ጥቅሞች መቋረጥ፣ እንደአግባቡ፣ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል። በተጨማሪ፣ በሜሪላንድ ህግ መሰረት፣ በMSDE ወይም በሌላ የስራ ፈቃድ ወይም የብቃት ምስክር ወረቀት ሰጪ የተሰጠው ማንኛውም ማረጋገጫ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል።

C. የአተገባበር ስልቶች

የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ወይም ተወካይ ይህን መመርያ ለመተግበር ቅደም ተከተሎችን እንደሚከተለው ያስቀምጣል፡

1. የተጠርጠረን የልጅ ማንሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት ዘገባና ምርመራ ቅደም ተከተል መመርያ ለመመስረት CPS፣ MCPD፣ እና የስቴት አቃቤ ፅ/ቤት/State's Attorney's Office ከሚያካትት የካውንቲ ሽሪክ ወኪል ድርጅቶች ጋር በመሆን የመግባባት ስምምነት መመስረትና መንከባከብ።

2. አንድ ወይም ከዚያ በላይ የMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ ማንሳቆል ተጠሪዎች መሰየም እና የማንሳቆል እና/ወይም የቸልተኝነት ዘገባ አርእስት ለሆነ ለማንኛውም ተማሪ የተቀነባበሩ አግልግሎቶች ለማቅረብ መመርያ መመስረት። ይህ የቅደም ተከተል መመርያ በየት/ቤት የሚመደቡ አገናኝ መኮንኖች፣ እናም አግባብ ያለቸው ፅ/ቤቶችና መምርያዎች ወኪሎችን ማካተት አለበት።

3. የCounty ሽሪክ ወኪል ድርጅቶችን ጨምሮ ከብሄራዊና ከአካባቢ ባለሙያዎች ከሚገኝ ድጋፍ ጋር፣ ይህን መመርያ ተግባራዊ ለማድረግ ለMCPS ሰራተኞች ተገቢ ሙያዊ ብልፅግና ማቅረብ፣ እና እንደ አግባቡ ለMCPS ስራ ተቋራጮችና በጎ-ፈቃደኞች የስልጠናና የመረጃ እድሎች መስጠት።

4. በMCPS ንብረት ወደሚገኙ ልጆች ቀጥተኛ፣ ተቆጣጣሪ የሌለው፣ እና መረን-የለሽ መዳረሻ ላላቸው አዲሶችንና ነባር ሰራተኞችን፣ እንዲሁም በጎ-ፈቃደኞችንና የውጭ ስራ ተቋራጮችን ላማጣራት ቅደም-ተከተሎች ማዳበር።

5. ለMCPS ሰራተኞችና ሌሎች በMCPS ንብረት ለሚገኙ በአዋቂዎችና በተማሪዎች መካከል መኖር ስለሚገባው ሀላፊነት ያለው ስነምግባርና ተገቢ ጠባይ ግልፅ መመዘኛዎች የያዘ የስነምግባር ደንብ ማዳበር።

6. የተማሪዎቻችንን ትምህርት ለመደገፍ በልጅ ማንሳቆል፣ የግል አካል ደህንነት፣ እና የጤና ትምህርት ከሂሎቶች ጠንካራ የትምህርት ቀጣይነት ማዳበር።

7. የወላጅ/አሳዳጊ እና የማህበረሰብ ትምህርትና ንቃት ፕሮግራም ማዳበር።

D. ተፈላጊ ውጤቶች

1. በሁሉም የMCPS ማህበረሰብ የልጆችንና የደካማ አዋቂዎችን መንሳቆልና ቸልተኝነት ለማወቅ፣ ዘገባ ለማቅረብ፣ እና ለመከላከል ትጉህ ጠባቂ ጥረቶች አማካይነት ለሁሉም ተማሪዎች ሰላማዊ፣ የሚማርክ፣ እና ደጋፊ አካባቢ ይቀርባል።

2. የMCPS እና የCounty ሽሪክ ወኪል ድርጅቶች የተጠረጠረ ማንሳቆልና ቸልተኝነት ዘገባዎችን ለማጣራት እና የተጠረጠረ ማንሳቆልና እና/ወይም ቸልተኝነት ዘገባዎች አርእስት የሆኑ ልጆችን ለመደገፍ በቀልጣፋነትና በውጤታማነት ይተባበራሉ።

E. ድህረ እይታ እና ዘገባ

የዚህ መመርያ ትግባሬ በሚከተሉት አመልካቾች ይገለፃል፡

1. የመረጃ አርእስቶች በመሆን ይህን መመርያ ለመተግበር የተዘጋጁ ቁልፍ መመርያዎች ለቦርድ ይላካሉ።

2. የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የሚከተሉትን የሚያካትቱ አመታዊ ሪፖርር እና እንዳስፈላጊነቱ ወቅታዊ መግለጫዎች ለቦርዱ ያቀርባል፡

   a) በMCPS ለህግ አስከባሪዎች ወይም ለመከላከያ አገልግሎቶች ወኪል ድርጅቶች የተመለከቱ የተጠረጠሩ የማንሳቆልና እና/ወይም የቸልተኝነት ጉዳዮች ቁጥር።

   b) በMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች የተጠረጠሩ የማንሳቆልና እና/ወይም የቸልተኝነት የሚመለከት የተጠናቀረ ዘገባ የሚከተሉትን የሚያካትት፡-

      i. በMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች የተጠረጠሩ የማንሳቆልና እና/ወይም የቸልተኝነት የሚያካትት በMCPS የቀረቡ ዘገባዎች ቁጥር፣ እና የነዚያ ዘገባዎች መጨረሻ ሁኔታ ማጠቃለያ በተወሰደ እርምጃ አይነት።

      ii. በማንሳቆልና እና/ወይም በቸልተኝነት ምክንያት በMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ የደረሰ እስራት ወይም የተመሰረተ ክስ፣ ለህዝብ ክፍት በሆኑ ሰነዶች የተመሰረተ ማጠቃለያ መግለጫ እንዲሁም የያንዳንዱ ሂደት ማሳረጊያ ማጠቃለያ።

      iii. የምስክር ወረቀቶች ወይም የስራ ፈቃዶች እንዲነሱ የሚጠይቁ በት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ለሜሪላንድ የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የተላኩ ደብዳቤዎች ቁጥር፣ እርምጃው እንዲወሰድ መነሾ በሆኑ ምክንያቶች በፈርጅ ተለያይተው።

   c) በክፍል C እላይ የተቀመጡ ስልቶች ትግባሬ.

   d) የልጅ ማንሳቆልና እና/ወይም ቸልተኝነትን በሚመለከት በMCPS እና በCounty ሽሪክ ወኪል ድርጅቶች መካከል የተከናወኑ የትብብሮሽ ጥረቶች መረጃ።

3. ይህ መመርያ በየአመቱ ድህረ እይታ ይደረግበታል/ይገመገማል።

የመመርያ ታሪክ፡ ውሳኔ ቁ. 137-80፣ ፌብሩወሪ 12፣ 1980 በውሳኔ ቁ. 853-83 ኦክቶበር 11፣ 1983 የተሻሻለ፣ በውሳኔ ቁ. 333-86፣ ጁን 12፣ 1986 የተሻሻለ፣ እና በውሳኔ ቁ. 458-86፣ ኦገስት 12፣ 1986 የተሻሻለ፣ በውሳኔ ቁ. 518-86፣ ሰፐተምበር 22፣ 1986 ተቀባይነት ያገኘ፤ በኦክቶበር 10፣ 2007 የተገመገመ፤ በውሳኔ ቁ. 359-15፣ ጁን 29፣ 2015 የተሻሻለ።